# ትንቢተ ዘካርያስ (56)

## ጥናት አንድ ዘካርያስ 1፡1-2፡13

የጥናት ዓላማ፦ የእስራኤልን ያስደነገጠና ሰባብሮ የጣለው እግዚአብሄር፤ ዛሬም ቢሆን አንገታችንን ቀና አድርገን እንዳንሄድና ዘወትር ተስፋ በቆረጠ መንፈስ እንድንመላለስ ለማድረግ የሚነሳብንን ጠላት ለማስደንገጥና እንዲሁም ቀንዶቹን ሰብሮ ለመጣል ከእኛ ጎን መኖሩን መረዳት እንደሚኖርብን ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ "እነዚህ ቀንዶች ማንም ራሱን ቀና ማድረግ እንዳይችል ይሁዳን የበታተኑ ናቸው፤ እነዚህ የእጅ ሙያተኞች ግን የመጡት እነርሱን ሊያስደነግጧቸው፤ ሕዝቡን ለመበተን በይሁዳ ምድር ላይ ቀንዳቸውን ያነሱትን የእነዚህን የአህዛብ ቀንዶች ሰብሮ ለመጣል ነው አለኝ።" ዘካ 1፡21

1. ትንቢተ ዘካርያስ 1፡1-2፡13 በአንድነት ይነበብ። በእዝራ 5፡1 እና በነህምያ 12፡16 ላይ እንደምናነበው ዘካሪያስን የአዶ ልጅ በማለት ይጠሩታል፤ በቁ1 ላይ ስንመለከት ግን አዶ አያቱ እንጂ የዘካርያስ አባቱ በራክዩ እንደሆነ እናነባለን፤ ታዲያ እዝራና ነህምያ ያንን ያሉት በስህተት ነው ወይስ ሌላ ምክንያት አለ ብለህ ታምናለህ? በቁ2ትና 3ት ላይ እግዚአብሄር አምላክ በነብዩ በኩል ለሕዝቡ አንድ ጥሪ ሲያስተላልፍ እንመለከተዋለን፤ በዚህ ጥሪ ውስጥ እግዚአብሄር ፊቱን ወደ ህዝቡ ለመመለስ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ የተነገረው ነገር ምንድነው?
2. በቁ4-6 ላይ ስናነብ፤ በዚያን ጊዜ ዘካሪያስ ትንቢቱን በሚተነብይላቸው ሕዝቦችና የእነርሱ አባቶች በነበሩት መሃል እያነጻጸረ ሲናገር ነው የምናየው፤ በእነዚህ ሶስት ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት፤ የአባቶቻቸውን ሁኔታ ተመልክተውና ከእነርሱ ተምረው ከአባቶቻቸው የተለየ ምን ዓይነት እርምጃ እንዲወስዱ ነው ነብዩ የሚያበረታታቸው? በቁ6 ላይ ከምናነበው በመነሳት፤ ነብዩ ዘካሪያስ ለህዝቡ ያስተላለፈው የትንቢት መልዕክት ምን ያህል በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቷል ብለህ ታምናለህ? ለምን ይህንን ማለት እንደቻልክ አስረዳ።
3. በቁ12-13 ላይ "የእግዚአብሄር መልአክ" በመባል የሚጠራው እግዚአብሄር ለሰባ ዓመታት ሙሉ ስለተቆጣቸው ስለኢየሩሳሌምና ይሁዳ ላቀረበለት ጥያቄ እግዚአብሄር ጸባዖት የመለሰለት በምን ዓይነት መንገድ እንደሆነ ነው የሚናገረን? በቁ14-17 ውስጥ ደግሞ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ የሚሆኑትን ነገሮች አስፍሯል፤ በቁ12-13 ላይ የምንመለከተው ከዘካሪያስ ጋራ ይነጋገር የነበረው የእግዚአብሄር መልዓክ ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ ይሁዳ ለጠየቀው ጥያቄ በቁ14-17 ውስጥ ያገኘው ምላሽ ምን የሚል ነው? አንተም ወደ አምላክህ ያቀረብከው ጥያቄህ እንደከንቱ እንደማይቀርና በጊዜው መልስ እንደሚመጣልህ በእምነት ልትጠብቀው ይገባሃል።
4. ቁ18-21ድን ስናነብ ነብዩ ዘካርያስና መልዓኩ ያደረጉትን የጥያቄና መልስ ምልልስ እንመለከታለን። ዘካርያስ በዚህ ክፍል ውስጥ በተለይም በቁ18-19 ላይ ያየውና ለአዕምሮው ጥያቄ ፈጥሮበት ለመልዓኩ ያቀረበለት ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? ነብዩ መልዓኩን ለጠየቀው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ምን የሚል ነበረ?
5. በ2፡1-2 ውስጥ ዘካሪያስ ወደ ላይ ሲመለከት ሌላ ነገር ያይና እንደገና ላልገባው ነገር ጥያቄን ሲጠይቅ ይታያል። በዚህን ጊዜ ዘካርያስ በፊት ለፊቱ ሲሆን የተመለከተው ነገርና የጠየቀው ጥያቄ ምን የሚል እንደነበረ ተናገር። በፊቱ ያየው ሰው ለጥያቄው ምን በማለት ነው መልስ የሚሰጠው?
6. ቁ3-6 ላይ ስንመለከት "ሩጥና ለዚህ ጎልማሳ እንዲህ ብለህ ንገረው" የሚለው የመልዓኩ አነጋገር ብቻ በመመልከት፤ ለዘካርያስ ወይም ለኢየሩሳሌም ሊደርስ ስለተፈለገው መልዕክት የሚነግረን አንድ እውነት ምንድነው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ኢየሩሳሌም ቅጥር እንደማይኖራት ሲነገር፤ ይህች ከተማ ማንም የፈለገ ሁሉ ዘው ብሎ የሚገባባትና የሚወጣባት፣ ለጠላትም ደግሞ የተጋለጠች ትሆናለች ማለት ነው ወይስ ይህ አነጋገር የተለየ ትርጉም አለው ብለህ ታምናለህ? በራስህ ከምታጥረው አጥር የተሻለና ጠላትህ ወዳንተ እንዳይቀርብ የሚከለክልልህ አስተማማኝ የሆነው አጥር እግዚአብሄር እንደሆነ አትዘንጋ። መዝ 61:3ትን ተመልከት
7. በቁ7-13 ውስጥ ታነብ ለጽዮን ልጅ እልልታና ደስታ እንደሚያመጣላት የተነገረው ነገር ምንድነው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር ለኢየሩሳሌም ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄን እንደሚያደርግላት ለመግለጽ ከተጠቀመባቸው አነጋገሮች መሃል በአንተ አመለካከት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውና ዋነኛ የምትለው ሃሳብ የትኛው ሃሳብ እንደሆነ ተናገር።
8. በቁ20-21 ውስጥ ስንመለከት እነዚህ ዘካርያስ የተመለከታቸውን አራቱ ቀንዶች የእግዚአብሄርን ሕዝብ አንገት የሚያስደፉና ሕዝቡ ቀና ብሎ መሄድ እንዳይችል የሚያደርጉ እንደነበሩ እናነባለን፤ ታዲያ እግዚአብሄር አምላክ የእጅ ባለሞያዎቹን ስለላከበት ምክንያት ይህ ክፍል ምን ይነግረናል? አንተንስ በጠላትህ ፊት አንገትህን እንድትደፋና በእግዚአብሄር ፊት ቀና ብለህ እንዳትሄድ የሚከለክልህ ነገር አለ ወይ? ዛሬም ቢሆን እግዚአብሄር አምላክ አንገታችንን ቀና አድርገን እንዳንሄድና ዘወትር ተስፋ በቆረጠ መንፈስ እንድንመላለስ ሊያደርግብን በእኛ ላይ የሚነሳውን ጠላታችንን ለማስደንገጥ እንዲሁም ቀንዶቹን ሰብሮ ለመጣል ከእኛ ጎን መኖሩን መዘንጋት አያስፈልገንም።

# ጥናት ሁለት ዘካርያስ 3፡1-4፡14

የጥናት ዓላማ፡- ምን ጊዜም ቢሆን አማኞችን በመክሰስ የታወቀና ሐዋር ያው ዮሐንስ በራዕ 12፡10 ላይ “የወንድሞቻችን ከሳሽ” በማለት የሚጠራው ሰይጣን ለሚሰነዘርብን ክስ ሁሉ፤ በአብ ዘንድ ቆሞ ስለ እኛ ምላሽ የሚሰጥልን ሊቀ ካህናችን የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለልን መረዳት ወሳኝነት እንዳለው ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “እርሱም ሊቀ ካህኑን ኢያሱን በእግዚአብሄር መልዓክ ፊት ቆሞ፤ ሰይጣንም ሊከሰው በስተቀኙ ቆሞ አሳየኝ። እግዚአብሄርም ሰይጣንን፤ አንተ ሰይጣን እግዚአብሄር ይገሥጽህ፤ ኢየሩሳሌምን የመረጠ እግዚአብሄር ይገስጽህ…አለው።”

1. ትንቢተ ዘካርያስ 1፡1-21 በአንድነት ይነበብ። በዚህ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ በምንመለከተው ትዕይንት ውስጥ፤ በተለይ በቁ1-2 ላይ ስናተኮር የምናገኛቸው ተዋናኞች ማን ማን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። እነዚህ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ የምናያቸው ሁሉ በትዕይንቱ ውስጥ የተለያየ ሚና ሲጫወቱ ነው የምናየው፤ በተለይ በዚህ ሥፍራ ሰይጣን ሲጫወት የምናገኘው ሚናው ምን ነበረ? ራዕ 12፡10 ላይ ዮሐንስ በዚህ ሥፍራ ላይ ሰይጣን በኢያሱ ላይ እያደረገ ያለውን ነገር በመውሰድ፤ እርሱ እያደረገ ያለው ነገር ከኢያሱም ያለፈ እንደሆነ በማስገንዘብ ለሰይጣን የሰጠው ስም ምን የሚል ነው?
2. በራዕ 12፡10 ላይ የተመለከትነው ጥቅስ ባይኖርና ይህንኑ ክፍል ብቻ በመመርኮዝ ሰይጣን እየከሰሰ ያለው ኢያሱን ብቻ አለመሆኑን ለማስረዳት የምትችልበት ምን መንገድ ሊኖር እንደሚችል ተናገር።
3. በቁ3-5 ያሉትን ቁጥሮች ስናነብ ሊከሰው በእግዚአብሄር ፊት የመጣው ጠላቱ ሰይጣን እውነትም ለመክሰስ የሚያበቃው ተጨባጭ ነገር እንደነበረው የሚያረጋግጥልን ሃሳብ የሚታይህ ከሆነ የትኛው ሃሳብ እንደሆነ ለወገኖች አካፍል። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስንመለከት እግዚአብሄር ለኢያሱ ያደረገለት ነገር ከሃጥያት ማስወገድ ያለፈ እንደሆነ እንደሆነ ግልጽ ሆኖ ተጽፏል፤ ይህ ለኢያሱ ከሃጥያት ማስወገድ ባሻገር የተደረገለት ተጨማሪ ነገር ምንድነው ትላለህ? ሊቀ ካህኑን እንኳን ስለ ሃጥያት መክሰስ ከቻለ፤ እኛንማ ምን ያህል ስህተት ሊያገኝብን እንደሚችል ማሰብና፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምን ያህል እንደሚያስፈልገን ያመለክተናል።
4. ከቁ1-5 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የኢያሱን ቆሻሻ ልብስ መልበስ ማለትም ሃጥያተኛነቱን ተመልክተን እግዚአብሄር ግን ከዚያ ሁሉ አጽድቶ አዲስ ልብስን እንዳለበሰው አይተናል፤ በቁ6-7 ላይ ስንመለከት ደግሞ እግዚአብሄር ይህንን ካደረገለት በኋላ እርሱ ከሃላፊነት ነጻ እንዳልሆነ በማስገንዘብ ከዚህ በኋላ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅበት ይነግረዋል፤ በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር የኢያሱ ሃላፊነት ምን እንደሆነ ነው የሚነግረው? እነዚህን እግዚአብሄር በፊቱ ያኖረለትን ሃላፊነቶች በመጠበቅ ቢመላለስ ከእግዚአብሄር የተገባለት ሶስቱ ተስፋዎች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
5. ቁ8-10 ላይ በምናነብበት ጊዜ እግዚአብሄር ለኢያሱ የሚሰጠውን መመሪያና ትዕዛዝ እንዲሰሙ የፈለጋቸው ሌሎችም ሰዎች እንዳሉ እንመለከታለን፤ እነዚህ በዚህ ሥፍራ ለሊቀ ካህናቱ የሚሰጠውን መመሪያና ትዕዛዝ እንዲሰሙ የሚጠበቅባቸው ሰዎች እነማን ናቸው? እግዚአብሄር በዚህን ሰዓት ለኢያሱ እያስታወቀው ያለውን ቁም ነገር እርሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ደግሞ ማወቅ እንደሚያስፈልጋቸው መነገሩ፤ ይህ መልዕክት በአንድ ሰው ብቻ ሳይወሰን ለሁሉ እንዲደርስ አንገብጋቢ የሚሆንበት ምክንያት ለምንድነው?
6. ቁ1-5 ውስጥ ዘካርያስን ስንመለከት መልዓኩ ለሚያሳየው ነገር እስከ ከአሁን በፊትም መልዓኩ ላሳየው ነገሮች የወሰደውን የምላሽ ዓይነት እንመለከታለን፤ ዘካርያስ ላሳየው መልዓክ በዚህኛው ጊዜ የመለሰው ምላሽ ከሌላኛዎቹ ጋራ የሚመሳሰልበት አንዱና ዋነኛው መንገድ በአንተ አመለካከት ምንድነው ትላለህ? በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ ዘካርያስ ለጠየቃቸው ጥያቄዎች በሙሉ የተጠየቀው መልዓክ ዘካርስን ባለማወቁ ሲነቅፈውና ሲያጣጥለው ትመለከታለህ ወይ? አንተስ ጥያቄ የሚሆንብህን ነገር በእግዚአብሄር ዘንድ ለማቅረብና መልስ ለማግኘት ምን ያህል ሙከራ ታደርጋለህ?
7. በቁ1-5 ውስጥ በተመለከትነው በዘይት ማሰሮውና በመቅረዙ ምሳሌነት በመጠቀም በቁ6-9 ላይ እግዚአብሄር አምላክ በባርያው በዘካርያስ በኩል ለአገልጋዩ ለዘሩባቤል እንዲተላለፍለት የፈለገው ዋነኛው መልዕክት ምን የሚል ነበረ? የእግዚአብሄርን ቤት ለመስራት ከባቢሎን የተመለሰው ሕዝብ በጠላት ማስፈራራትና በተለያየ ምክንያት ተስፋ የቆረጠን ሕዝብ፣ በተለይም ደግሞ የዚህ ዓይነቱን ሕዝብ ተስፋ የቆረጥን ሕዝብ ካለበት ሁኔታ ውስጥ ለማውጣት፣ ይህ መልዕክት ለዘሩባቤል ምን ያህል ያስፈልጋል ብለህ ታምናለህ?
8. “እርሱም እነዚህ ሁለቱ የምድርን ሁሉ ጌታ ለማገልገል የተቀቡ ናቸው አለኝ” በማለት መልዓኩ ለዘካርስ በቁ14 ላይ የተነገረላቸው ሰዎችን ማንነት፤ ሕዝቡ ከምርኮ ከተመለሰ በኋላ በዚህ መንገድ ያገለገሉና እነርሱ ሊሆኑ ይችላሉ ብለህ በአንተ አመለካከት የምትላቸው ሁለት ሰዎች ማንና ማን እንደሆኑ ተናገር።
9. ሰይጣን ክሱን በኢያሱ ላይ በሚያቀርብበት ወቅት ከኢያሱ አንደበት አንዳችም ቃል እንዳልወጣ እንመለከታለን፤ ኢያሱ በእግዚአብሄር ፊት ለተከሰሰበት ክስ ምላሽን ሲሰጥ የምናየው ማንን ነው? ጠላትህ ለሚያመጣብህ ክስ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ፊት ቆሞ በአንተ ቦታ ምላሹን እንደሚሰጥልህ ምን ያህል ተረድተሃል? ከጠላታችን ለሚሰነዘርብን ክስ በአብ ዘንድ ሆኖ ምላሽ የሚሰጥልን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለልን ዘወትር ማስታወስ ተገቢና ወሳኝ ነገር ነው።

# <u>ጥናት ሶስት ዘካርያስ 6፡9-7፡14</u>

የጥናት ዓላማ፡- ለቤቴል ሰዎች እግዚአብሄር የመለሰላቸው መልስ ምንም እንኳን ለጊዜው ሊያሳምማቸው የሚችል ቢሆንም እንኳን ጥያቄአቸውን ወደ ትክክለኛው ቦታ እንደወሰዱ ሁሉ፤ እኛም መልሱ የሚስማማንም ይሁን የማይስማማን፤ ጥያቄ ሲኖረንና መልስን በምንፈልግበት ጊዜ መሄድ የሚኖርብን ወደ ሰዎች ሳይሆን ለጥያቄአችን ሁሉ መልስ ወዳለው ወደ እግዚአብሄር መሆን እንደሚኖርበት ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "የቤቴል ሰዎች እግዚአብሄርን ለመለመን…ላኩ፤ እነርሱም የእግዚአብሄር ጸባዖት ቤት ካህናትና ነብያት፣ ብዙ ዓመት እንዳደረግሁት፣ በአምስተኛው ወር ማዘንና መጾም ይገባኛልን? ብለው ጠየቁ።" ዘካ 7፡2-3

1. ትንቢተ ዘካርያስ 6፡9-7፡14 በአንድነት ይነበብ። በዘካ 6፡9-11 ውስጥ እግዚአብሄር ለዘካሪያስ ትንቢት ከመናገር ያለፈ ትዕዛዝ ሲሰጠው እንመለከታለን። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ነብዩ ዘካሪያስ ያደርገው ዘንድ ከእግዚአብሄር የተሰጠው ትዕዛዝ ምን ነበረ? በ2ኛ ዜና 26፡16-20 ውስጥ ስለ ንጉሱ ዖዝያን የተጻፈውን በማንበብ፣ በዚያን ሰዓት ደግሞ ካህናቱ የተናገሩትን፣ በተጨማሪም ደግሞ እግዚአብሄር የወሰደውን እርምጃ ሁሉ በመመልከት፤ በዘካ 6፡11 ላይ "…አክሊል ሥራ፤ በኢዮሴዴቅ ልጅ በሊቀ ካሕኑ ራስ ላይም አድርገው።" የሚለውን እግዚአብሄር ለዘካርያስ የሰጠውን ትዕዛዝ ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
2. በዘካ 3፡8፣ በኢሳ 4፡2፣ 11፡1፣ ኤር 23፡5፣ 33፡15 እና የመሳለሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስንመለከት፤ በዘካ 6፡12 ላይ የምንመለከተውን "ቅርንጫፍ" በመባል የተጠራው የሚናገረው ስለማን እንደሆነ ሃሳብ ማግኘት እንችላለን፤ ይህ በዚህ ሥፍራ ላይ "ቅርንጫፍ" በማለት እግዚአብሄር የሚናገርለት ሰው፤ ከተለያዩት ጥቅሶች በመነሳት ይህ ሰው ማን ነው ብለህ ታምናለህ?
3. በቁ12 እና በቁ13 መጀመሪያ ላይ ደግሞ ይህ ቅርንጫ ተብሎ የተጠራው "የእግዚአብሄርንም ቤተ መቅደስ ይሰራል፤ የእግዚአብሄርን ቤተ መቅደስ የሚሰራው እርሱ ነው" ይላል። በዘካ 4፡9 ላይ እንደምናነበው ከሆነ በአሁን ሰዓት እየተገነባ ያለውን የጀመረው ዘሩባቤል እንደሆነና እርሱ ራሱ ደግሞ እንደሚጨርሰው ተነግሯል፤ ታዲያ በዚህ ሥፍራ ላይ የተነገረለትና ይህ ሰው የሚሰራው ቤተ መቅደስ የትኛው ነው? በ2ኛ ዜና 26 ውስጥ የተመለከትነው ታሪክ በምን መንገድ ነው በዘካ 6፡13 ላይ የተነገረውን ሃሳብ ሊያጎላልን የሚችለው?
4. በዘካርያስ ምዕራፍ 6 ውስጥ በኢያሱ ራስ ላይ የተደረገው አክሊል በእግዚአብሄር አይን ሌላ ዓላማ እንደነበረው ከቁ14 መረዳት እንችላለን። ይህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምናየውና በሊቀ ካህናቱ ራስ ላይ እንዲደረግ እግዚአብሄር ዘካርያስን ያዘዘው አክሊል እውነተኛ ዓላማው ወይም ደግሞ በዚህ ድርጊት ውስጥ እግዚአብሄር ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምን ነበረ?
5. 7፡4-7 ላይ እግዚአብሄር ለቤቴል ሰዎች ምላሽ የሰጠበትን አነጋገር ስንመለከት፤ በአዲስ ኪዳን ጳውሎስ በሮሜ 14፡6 ላይ ከሚናገረው መመሪያ ጋራ የሚስማማው በምን መንገድ ይመስልሃል? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ጥያቄ ላቀረቡለት ሰዎች መልሶ በጥያቄ ሲመልስላቸው፤ በተለይም በቁ7 ላይ "ኢየሩሳሌምና በዙሪያዋ ያሉ ከተሞች በሰላምና በብልጽግና ላይ ሳሉ… እግዚአብሄር በቀዱሙት ነብያት የተናገረው ቃል ይህ አልነበረምን?" በማለት የጠየቃቸው ጥያቄ የቀደሙት ነብያት የተናገሩትና የምታስታውሳቸውን ጥቅሶች ተናገር። እግዚአብሄርን ለማምለክ እርሱ በመረጠው መንገድ እንጂ የራሳችንን መንገድ መርጠን እርሱን እያመለኩት ነው ማለት አንችልም።
6. ከቤቴል ተልከው ለመጡት ሰዎች እነርሱ ያሉበትን ሁኔታ በቀጥታ ከቀደሙት አባቶቻቸው ሕይወት በመነሳት በቁ8-10 ላይ ይናገራቸዋል ። የቀደሙት ሰዎች እግዚአብሄር በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ለተሰጣቸው መመሪያ ምላቻቸው ምን እንደነበረ ነው ቁ11-12 የሚያሳየን? የቀደሙት ሰዎች በመባል እግዚአብሄር እንደምሳሌ የሚሰጣቸው ሰዎች፤ እግዚአብሄር እንድታመልኩኝ የምፈልገው በዚህ መንገድ ነው ባለበትና እነርሱ ደግሞ ያንን ወዲያ ጥለው በራሳቸው መንገድ በመሄዳቸው የተሰማው ስሜት ምን ነበረ?
7. በቁ13 እና በቁ14 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር ለሰጣቸው የአምልኮ መመሪያ ሕዝቡ የእንቢተኛነትን ምላሽ በመስጠታቸው እግዚአብሄር የተሰማውን ስሜት ከላይ የተመለከትናቸው ቁጥሮች አሳይተውናል። ለሕዝቡ እንቢተኛነትና ለእግዚአብሄር ለመታዘዝ ባለመፍቀድ ምክንያት እግዚአብሄር ለመውሰድ የተገደደው እርምጃ ምን ነበረ?
8. ዘካ 7፡1-3ትን መለስ ብለን ስንመለከት፤ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በምርኮ አገር የሚገኙት የቤቴል ሰዎች ሲያደርጉ የምናገኛቸው ምን ሲያደርጉ ነው? እግዚአብሄር ለቤቴል ሰዎች የሰጠው ምላሽ ምናልባትም ከሚጠብቁት የተለየ እንደሚሆን እናያለን፤ ታዲያ ምላሹ እንደጠበቁት ሆኖ ባይገኝም እንኳን እነዚህ ሰዎች አንድ መልካም ነገር አድርገዋል ማለት የሚያስችለን ሃሳብ ምን እናያለን? አንተስ ጥያቄህን የምትወስደው ወደ ሰዎች ነው ወይስ ወደ እግዚአብሄር? መልሱ ምንም ዓይነት ይሁን፤ ጥያቄ ሲኖረንና መልስን ስንፈልግ መሄድ የሚኖርብን ወደ ሰዎች ሳይሆን ለጥያቄአችን ሁሉ መልስ ወዳለው ወደ እግዚአብሄር መሆን ይኖርበታል።

# ጥናት አራት ዘካርያስ 8፡1-23

የጥናት ዓላማ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕይወታችን ሲመጣና መኖሪያውን በእኛ ውስጥ ሲያደርግ፤ ከቀደመው ከፈራረሰውና ባድማ ከሆነው ሕይወት ውስጥ አውጥቶ በእውነትና በቅድስና በታጀበ ሕይወት እንድንመላለስ ሊያደርገን እንደሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እግዚአብሄር እንዲህ ይላል፤ ወደ ጽዮን እመለሳለሁ፤ በኢየሩሳሌም እኖራለሁ፤ ኢየሩሳሌም የእውነት ከተማ ትባላለች፤ የእግዚአብሄር ጸባዖት ተራራም ቅዱስ ተራራ ይባላል።"

1. ትንቢተ ዘካርያስ 8፡1-23 በአንድነት ይነበብ። ቀደም ባለው ምዕራፍ ማለትም በምዕ7 ውስጥ አባቶቻቸው ለእግዚአብሄር ለመታዘዝ እንቢ በማለታቸው የተነሳ እግዚአብሄር ራሱ ምድሪቱን ባድማ እንድትሆን እንደፈቀደ በተለይም በቁ13-14 ውስጥ ማየት እንችላለን። ታዲያ እግዚአብሄር በቁ1ና በቁ2ት ላይ ስለ ጽዮን ከተማ እንደቀና መናገሩ በምን ምክንያት ሊሆን ይችላል ብለህ ታምናለህ?
2. የእግዚአብሄር ወደ ጽዮን መመለስና በኢየሩሳሌም ውስጥ የማደሩ ውጤት ሆነው በቁ4-5 ውስጥ የተነገሩ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን መመልከት እንችላለን፤ እነዚህ ሁለቱ የእርሱ የመገኘት ውጤቶች የሆኑት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ተጠቅሶ የሚገኘው የእግዚአብሄር በከተማይቱ ውስጥ የመገኘትና በእርሷ ውስጥ የማደሩ ውጤት የሆነው ነገር በምን መንገድ ይመስልሃል እንደበረከት ተደርጎ መቆጠር የሚችለው?
3. በቁ6 ላይ "በዚያን ጊዜ ይህ ለቀረው የእስራኤል ህዝብ አስደናቂ መስሎ ሊታይ ይችላል…" በማለት እግዚአብሄር ሲናገር እንሰማዋለን። ሰዎች አርጅተው በምርኩዝ መሄዳቸው ወይም ደግሞ ልጆች ተወልደው በአደባባይ ላይ መንጫጫታቸው ለእስራኤል ሕዝብ እንደ አስደናቂ ነገር ሆኖ የሚታይበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል? በቁ7-8 ላይ ስናነብ "እታደጋለሁ"፣ "አመጣቸዋለሁ"፣ "አምላካቸው እሆናለሁ" የሚሉት አነጋገሮችን ሁሉ ስንመለከት፤ ለእስራኤል ሕዝብ ሊሆንለት ላለው መልካም ነገር ሁሉ መነሻና ምንጩ ማን እንደሆነ ነው የሚጠቁመን? በአንተ ሕይወት ውስጥስ ለምታየው በረከት ሁሉ ምንጩ ማን እንደሆነ ትገነዘባለህ ወይ?
4. ቁ9-11ድን ስናነብ፤ በዚያን ሰዓት ነብዩ ዘካርያስ የእግዚአብሄር ሕዝብ የአምላኩን ቤተ መቅደስ ተነስቶ እንዲሰራ እጁን እንዲያበረታ ለማበረታታት እየተናገረ ያለውን መልዕክት እግዚአብሄር አምላክ እያነጻጸረ የሚናገረው ከየትኛው ጊዜ ትንቢት ጋራ ነው? ይህ የእስራኤል ቅሬታ የሆነውና ከባቢሎን የተመለሰው ሕዝብ ወደዚህች ምድር ከመምጣቱ በፊት በዚህች ምድር ላይ ይኖሩ በነበሩት ሰዎች ላይ ይደርስ ስለነበረው ነገር እነዚህ ቁጥሮች ምን ይነግሩናል?
5. በቁ12-13 ላይ እግዚአብሄር ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ለመጡት ሰዎች በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ያዘጋጀላቸውን የበረከት ዓይነቶች በመዘርዘር ይነግራቸዋል፤ በዚህ ቦታ ቃል የገባላቸው በረከቶች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። እግዚአብሄር ከስደት አገር ለተመለሰው ሕዝቡ በብዙ ዓይነት በረከቶች ሊባርካቸው እንደተዘጋጀ ቀደም ብለን ተመልክተናል፤ ሆኖም ከእነርሱ የሚጠብቀውን አንድ ነገር ብቻ እንዳለም በእነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ እንመለከታለን፤ ይህ አንድ ነገር ምንድነው? አንተ ዝም ብለህ የእግዚአብሄርን ሥራ ለመሥራት ትጋትህን ቀጥል፤ በረከትን አስመልክቶ ግን እግዚአብሄር መባረክን ስለሚያውቅበት ለእርሱ ተውለት።
6. ከቁ14-19 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ከምናነበው፤ የእግዚአብሄርን የወደደውን ነገር ለማድረግ ከልካይ እንደሌለው፣ ክፉ ሆነ በጎ ለማድረግ ሁሉ ነገር ሁሉ በእርሱ ፈቃድ የሚሄድ እንደሆነ የሚጠቁመን የትኛው ሃሳብ ነው? እግዚአብሄር ጸባዖት ለሕዝቡ ከአሁን በኋላ እንዲያደርጓቸው የሚፈልጋቸውን ነገሮች ግልጽ ባለ መንገድ ዘርዝሮ ሲናገራቸው እንመለከታለን። በተለይም በቁ16 እና በቁ17 ላይ ተዘርዝረው የምናገኛቸውና ከሕዝቡ እንደሚጠብቅ የተናገራቸው ቢያንስ አራት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
7. በቁ3 ላይ እስራኤል በእግዚአብሄር በመካከላቸው መገኘትና በኢየሩሳሌም በማደሩ ምክንያት የተገኙትን በረከቶች፤ በምን መንገድ ነው በቁ20-23 ውስጥ ከምናነበው አህዛብ ሊያገኙ ካሉት በረከቶች ጋራ ማገናኘት የምንችለው?
8. በቁ3 ላይ ስንመለከት ኢየሩሳሌም "የእውነት ከተማ" እንድትባል፤ የተራራውም ስም "ቅዱስ ተራራ" በመባል ስማቸው እንደሚለወጥ ነብዩ ዘካርያስ ይነግረናል። በዚህ ቁጥር ላይ ስናነብ፤ ለከተማይቱ ስምና እንዲሁም ለተራራው ስም የመለወጥ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድነው? የኢየሱስ ክርስቶው ወዳንተ መምጣትና በአንተ ውስጥ መኖር በሕይወትህ እውነተኛነትንና ቅድስናን ወልዷል ወይስ ከቀድሞው ልዩነት አይታይብህም? ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕይወታችን ሲመጣና መኖሪያውን በእኛ ውስጥ ሲያደርግ፤ ከቀደመው ርካሽና የማይረባ ሕይወት አውጥቶ በእውነት በቅድስና የታጀበ ሕይወት እንድንለማመድ ሊያደርገን እንደሆነ መዘንጋት አይኖርብንም።